# የልዩ ስልጠና (THEME) ት/ቤቶች

## ክፍሎች፡- ከቅድመ-መዋዕለ ህጻናት እስከ ስምንተኛ ክፍል

## 2019 - 2020 ምዝገባ ክፍት የሚሆነው፡-

## ጃንዋሪ 7፣ 2019 - ፌብርዋሪ 8፣ 2019

SCHOOL CHOICE (የት/ቤት መምረጫ)

### የት/ቤት መምረጫ ድረገጽ፡-

http://dekalbschoolsga.org/school-choice

### በሚከተለው አድራሻ በድረገጽ ያመልክቱ፡-

* http://www.yourchoicedekalb.org

**የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች**

* Edward L. Bouie, Sr.
* Marbut
* Narvie J. Harris
* Oakcliff
* Robert Shaw
* Wynbrooke

**መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

* The Champion School

የክፍት ምዝገባ ት/ቤት ምርጫ ድጋፍ ሰጪ አድራሻ፡-

**1192 Clarendon Avenue**

**Avondale Estates, GA 30002**

*ጃንዋሪ 7፣ 2019 - ፌብርዋሪ 8፣ 2019*

*9:00 ኤ.ኤም - 4:00 ፒ.ኤም*

የዘገየ ምዝገባ ት/ቤት ምርጫ፡-

ፌብርዋሪ 9፣ 2019 – ኦገስት 31፣ 2019

የእጣ ውጤቶች የሚወጡት፡- ማርች 22፣ 2019 @ 5:00 ፒ.ኤም

# የልዩ ስልጠና ት/ቤቶች መረጃ

| የልዩ ስልጠና ት/ቤቶች | አድራሻ | የትምህርት ሰዓታት | የጉዙ ቀኖችና ሰዓታት | የልዩ ስልጠና ተማሪ አቅራቢ ት/ቤቶች |
|---|---|---|---|---|
| **Edward L. Bouie Sr. መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>ቅድመ-መዋለ ህጻናት - 5 | 5100 Rock Springs Road<br>Lithonia, GA 30038<br>(678) 676-8202 | 7:45 ኤ.ኤም<br>-<br>2:15 ፒ.ኤም | ጃንዋሪ 17፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - እኩለ ቀን<br>ጃንዋሪ 24፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - እኩለ ቀን<br>ጃንዋሪ 31፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - እኩለ ቀን | Browns Mill ES<br>Fairington ES<br>Flat Rock ES<br>Murphey Candler ES |
| **Narvie J. Harris መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>ቅድመ-መዋለ ህጻናት - 5 | 3981 McGill Drive<br>Decatur, GA 30034<br>(678) 676-9202 | 7:50 ኤ.ኤም<br>-<br>2:15 ፒ.ኤም | ጃንዋሪ 16፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 17፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 18፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም | Chapel Hill ES<br>Cedar Grove ES<br>Oak View ES |
| **Marbut መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>ቅድመ-መዋለ ህጻናት - 5 | 5776 Marbut Road<br>Lithonia, GA 30058<br>(678) 676-8802 | 7:30 ኤ.ኤም<br>-<br>2:05 ፒ.ኤም | ጃንዋሪ 10፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 17፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 31፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም | Panola Way ES<br>Redan ES<br>Stoneview ES<br>Woodridge ES |
| **Oakcliff መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>ቅድመ-መዋለ ህጻናት - 5 | 3150 Willow Oak Way<br>Doraville, GA 30340<br>(678) 676-3102 | 7:45 ኤ.ኤም<br>-<br>2:15 ፒ.ኤም | ጃንዋሪ 10፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 17፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 31፣ 2019<br>9:00 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም | Dresden ES<br>Pleasantdale ES<br>Cary Reynolds ES |
| **Robert Shaw መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>ቅድመ-መዋለ ህጻናት - 5 | 385 Glendale Road<br>Scottdale, GA 30079<br>(678) 576-6002 | 7:45 ኤ.ኤም<br>-<br>2:15 ፒ.ኤም | ጃንዋሪ 11፣ 2019<br>8:30 ኤ.ኤም - 9:30 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 18፣ 2019<br>8:30 ኤ.ኤም - 9:30 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 25፣ 2019<br>8:30 ኤ.ኤም - 9:30 ኤ.ኤም | Allgood ES<br>Avondale ES<br>Dunaire ES<br>Hambrick ES<br>Indian Creek ES<br>Jolly ES<br>McLendon ES<br>Rockbridge ES<br>Rowland ES |
| **Wynbrooke መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>ቅድመ-መዋለ ህጻናት - 5 | 440 Wicksbury Way<br>Stone Mountain, GA 30087<br>(678) 676-5002 | 7:45 ኤ.ኤም<br>-<br>2:15 ፒ.ኤም | ጃንዋሪ 16፣ 2019<br>8:30 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>ጃንዋሪ 24፣ 2019<br>8:30 ኤ.ኤም - 10:00 ኤ.ኤም<br>Martes, 29 de enero de 2019<br>6:00 ፒ.ኤም - 7:30 ፒ.ኤም | Pine Ridge ES<br>Princeton ES<br>Rock Chapel ES<br>Shadow Rock ES |
| **Champion መካከለኛ ት/ቤት**<br>ክፍሎች፦<br>6 - 8 | 5265 Mimosa Drive<br>Stone Mountain. GA 30087<br>(678) 875-1502 | 8:50 ኤ.ኤም<br>-<br>3:50 ፒ.ኤም | Martes, 15 de enero de 2019<br>9:30 ኤ.ኤም - 11:00 ኤ.ኤም<br>Miércoles, 16 de enero de 2019<br>9:30 ኤ.ኤም - 11:00 ኤ.ኤም<br>Jueves, 17 de enero de 2019<br>9:30 ኤ.ኤም - 11:00 ኤ.ኤም | ሁሉም የዲካልብ መካከለኛ ት/ቤቶች |

**የተለመዱት የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች ታሪክ**
የዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት የተለመዱት የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች የጀመሩት በ1996 ሲሆን ቀደም ሲል በነበረ የትምህርት አፈፃፀም ለማይገደቡ ወላጆችና ተማሪዎች ተመራጭ ትምህርት ቤቶች ሆነው አገልግለዋል_ ይህ ፕሮግራም የተሻሉ ነገሮችን መጠበቅን፣ የወላጅ ተሳትፎንና ፈታኝ ትምህርት ሂደቶችን ለማለፍ ፈላጎት መኖርን መሰረት ያደረገ ፕሮግራም ነው። የዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ሰባት የተለመዱ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች ያሉት ሲሆን እነዚህም Edward L. Bouie፣ Sr., Marbut፣ Narvie J. Harris፣ Oakcliff፣ Robert Shaw፣ Wynbrooke Traditional ልዩ ስልጠና ት/ቤቶች፣ እና Champion Traditional ልዩ ስልጠና መካከለኛ ት/ቤት ናቸው። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ የዲካልብ ካውንቲ፣ በጆርጅያ ይገኛሉ።

**የተለመዱት የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች ክፍሎች**
የተለመደ የልዩ ስልጠና ት/ቤት የሚባለው የተማሪዎችንና የወላጆችን ፍላጎቶች ለማሟላት በቀረጻቸው ልዩ መገለጫዎች ምክንያት በዙሪያው ከሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በመላው የትምህርት ዲስትሪክቱ ውስጥ ከሚገኙ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን የሚስብ ትምህርት ቤት ነው። የተለመደ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ለተማሪዎች ጥልቅ እና በትምህርት አይነቶች መካከል መመጋገብን የሚፈጥር የትምህርት ፕሮግራም በተቀናጀ አወቃቀር እንዲያቀርብ ሆኖ የተነደፈ ትምህርት ቤት ነው። ፈታኝ በሆነው ፕሮግራም ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊዎች የሚሆኑ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቤት ውስጥ ጥናት ፕሮጀክቶችንና የዓለም ቋንቋዎችን እንዲተዋወቁ ማድረግን ያካትታል። የተለያዩ የትምህርት ስርዓቶችን የሚያካትቱ የትምህርት አሰጣጦች ምርምርን መሰረት ወደሚያደርጉ ስራዎች እና ተግባራዊ ፕሮጀክቶች የሚያዘነብሉ ሲሆኑ እነዚህም ችግር መፍታትንና በአፅንዖት ማሰብን ይጠይቃሉ። ወላጆች ትምህርታዊ ፕሮግራሙን ለማስረጽና ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ለማድረግ ስለሚሰሩ የፕሮግራሙ ወሳኝ አካል ናቸው።

**ለተለመዱ የመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት መጋቢ ትምህርት ቤቶች**
የተለመዱት የመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች በዋናነት የቦታ ጥበት ካለባቸው ትምህርት ቤቶች ይቀበላሉ። በአቅራቢያ ባሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉና እገዛ ለማግኘት ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች መጋቢ በመሆን ያገለግላሉ። የመጋቢ ትምህረት ቤቱ ምዝገባ ከቀነሰ፣ መጋቢ ትምህርት ቤቱ ለልዩ ስልጠናው መጋቢ መሆኑን ሊያቆም ይችላል። ይህ የመለየት ስራ በየዓመቱ ይደረጋል። የመካከለኛ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት በዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ተማሪዎችን ይቀበላል።

**የተለመደ የልዩ ስልጠና ትምህረት ቤት ልዩ መገለጫዎች**

- የወላጅ ተሳትፎ ይፈልጋል
- በወሳኝ የትምህርት አይነቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋል
- ከፍ ያለ የትምህርት መስፈርትና የተሻሉ ውጤቶችን መጠበቅ
- ከዓለም አቀፍ ቋንቋ ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ
- ጥብቅ የስነ-ምግባር መመሪያ
- አስገዳጅ የደንብ ልብስ/ጥብቅ የአለባበስ መመሪያ
- በአፅንዖት ማሰብን እና ችግር መፍታት ላይ ትኩረት ማድረግ
- አውቶማቲክ የማንበብ ፕሮግራም (የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች)
- አስገዳጅ የሆነ የክረምት ንባብና የሂሳብ እንቅስቃሴዎች
- አስገዳጅ የሆኑ ዕለታዊ የቤት ስራዎች
- የቱቶሪያል ፕሮግራሞች
- እንቅስቃሴን መሰረት ያደረጉ ትዕዛዞች
- «የአጀንዳ» እቅድ ማውጫዎች
- ሁሉንም የትምህርት አይነቶች የሚያስተሳስር የትምህርት አቀራረብ

**የተለመደ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት መመሪያዎች**

- ወላጆችና ተማሪዎች ለአንድ አመት የሚቆይ የምዝገባ ግዴታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል
- ከቅበላ በኋላ፣ ተማሪው ቦታውን/ዋን ላለማጣት በትምህርት መጀመሪያው ቀን ጀምሮ መገኘት አለበት/ባት
- በልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች ልጆቻቸውን ያስመዘገቡ ወላጆች የወላጅ ተሳትፎ አገልግሎት ሰዓቶችን ማሟላት አለባቸው። ከአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ ልጆች በመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤትና በመካከለኛ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት የተመዘገቡ ከሆነ፣ ወላጆች የወላጅ ተሳትፎ አገልግሎት ሰዓቶች እንዲያዙላቸው በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 50% የወላጅ ተሳትፎ አገልግሎት ሰዓቶችን ማሟላት አለባቸው።
- ተማሪዎች በተመዘገቡበት የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈለገውን የደንብ ልብስ መልበስ አለባቸው።
- በምዝገባው ለመቀጠል የወላጅ ተሳትፎ አገልግሎት ማጠናቀቅንና የተማሪው/ዋ በትምህርቱ ላይ መገኘትን ጨምሮ የልዩ ስልጠና ት/ቤቱን ደንቦችና ግዴታዎች ማክበርን ይጠይቃል።
- ሁሉንም የትምህርት ቤት ስራዎች እስከሚቻለው ድረስ በጥሩ ሁኔታ ማጠናቀቅ።
- ትምህርት ቤት አዘውትሮ መገኘትና በሰዓት መገኘት። ከልክ ያለፈ አቋርጦ መውጣትን ማስወገድ።
- የትምህርት ጊዜው ወይም በትምህርት ቤቱ የተፈቀደ እንቅስቃሴ እንዳበቃ የትምህርት ቤቱን ግቢ ወዲያውኑ ለቅቆ መውጣት።
- ለትምህርት ቤቱ አግባብነት ያለው ጸባይ ማሳየት።
- ተመዝግበው ያሉ እና የደንብ ጥሰት ያልተመዘገበባቸው ተማሪዎች በዚያ የልዩ ስልጠና ት/ቤት ፕሮግራም መሳተፋቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ።
- የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ምደባ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም በተወሰነው ቀን ምዝገባ ካልተደረገ፣ ተማሪው/ዋ በቀጣዩ ክፍት የምዝገባ ጊዜ እንደገና ማመልከት ይኖርበታል/ይኖርባታል።

**እነዚህ መመሪያዎች እስከተጠበቁ ድረስ፣ የተመዘገበ/ች ተማሪ ውጤታማ የትምህርት ጊዜ ያገኛል/ታገኛለች። እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟሉባቸው ሁኔታዎች፣ ተማሪው/ዋ በአካባቢው/ዋ በሚገኝ ትምህርት ቤት እንዲማር/እንድትማር ያስፈልጋል።**

***የምርጫ ሂደቱ አጭር ማብራሪያ***
የተለመዱ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት አመልካቾች በአውቶማቲክ የመምረጫ ሂደት ይመረጣሉ። ካሉት ቦታዎች በላይ የሆኑ አመልካቾች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ያልተመረጡት ተማሪዎች በመጠባበቅ ላይ ያሉ ዝርዝሮች ውስጥ ይገባሉ። ካሉት ቦታዎች ያነሱ አመልካቾች በሚኖሩበት ጊዜ፣ የዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ሁሉንም መስፈርት የሚያሟሉ አመልካቾች በልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ይመዘግባቸዋል። ይህ ሁኔታ ባለበት ጊዜ፣ ከቀነ ገደቡ በፊት የገቡ ማመልከቻዎችም ሊታዩ ይችላሉ። የተመረጡና በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ አመልካቾች በአውቶማቲክ የሚደረገው የምርጫ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

***ለልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ለማመልከት መስፈርት ስለማሟላት***

- ሁሉም የዲካልብ የግል ወይም የቤት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ከቅድመ መዋለ ህፃናት እስከ አምስተኛ ክፍል ድረስ ለመመዝገብ ዝግጁ የሆኑ እና በታወቀ የልዩ ስልጠና መጋቢ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መገኛ አካባቢ ነዋሪ ከሆኑ፣ በተወሰነው የተለመዱ የልዩ ስልጠና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመግባት በዕጣ ማውጣቱ ሂደት ለመሳተፍ ማመልከት ይችላሉ። የማመልከቻ ቀነ-ገደቡ ከማለፉ በፊት የትምህርት ቤት ምርጫ ማመልከቻውን በድረ ገጽ አመልክተው መሆን አለበት።

- ሁሉም አሁን ያሉት የዲካልብ፣ የግል እና የቤት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሆነው 6ኛ፣7ኛ እና 8ኛ ክፍል የሚመዘገቡና የዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ነዋሪ የሆኑ ተማሪዎች ለተለመዱ የልዩ ስልጠና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ መስፈርት ያሟላሉ። የማመልከቻ ቀነ-ገደቡ ከማለፉ በፊት የትምህርት ቤት ምርጫ ማመልከቻውን በድረ ገጽ አመልክተው መሆን አለበት።

- በልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት የተመዘገቡ ከአንድ በላይ የሆኑ የአንድ ቤተሰብ አባል ተማሪዎች ወላጃቸው የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ማመልከቻውን በቀነ-ገደቡ እስካስገቡላቸውና ተማሪዎች ለልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቱ መስፈርት የሚያሟሉ እስከሆኑ ድረስ በምርጫ ሂደቱ መሳተፍ ይችላሉ።

- ትምህርት ቤቱ መጋቢ ትምህርት ቤት መሆኑ ካበቃ፣ አዳዲስ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት ቤት አይመዘገቡም፤ ነገር ግን፣ የነባር ተማሪ እህት/ወንድም የሆነ/ች ተማሪ በትምህርት ቤቱ ለመመዝገብ ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች።

***የትምህርት ሰዓታት እና የትምህርት ዓመት***
የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች የስራ ሰዓታት እና ካሌንደሮች ብዙ ጊዜ ከተለመደው የትምህርት ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። እንደሁኔታው የተራዘመ የቀን ፕሮግራሞች፣ እንቅስቃሴዎች እና ቱቶሪያሎች ሊኖሩ ይችላሉ።

***ትራንስፖርት***
በጣም የቅርብ ጊዜው የዲካልብ ካውንቲ የትራንስፖርት ፖሊሲ ተግባር ላይ ይውላል። ለወላጆች፣ ለልዩ ስልጠና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አሁን ባለው አወቃቀር መሰረት የሚቀጥል መሆኑን ልብ ይበሉ። የመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከሰፈራቸው እስከተመረጠው ትምህርት ቤት ድረስ የትራንስፖርት አገልግሎት መቅረቡ ይቀጥላል። የቻንፒዮን ልዩ ስልጠና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት መጓጓዣ አሁን ባለው አወቃቀር ይቀጥላል። በወቅቱ የትምህርት ዓመት፣ የመካከለኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወደ የቻንፒዮን ልዩ ስልጠና መካከለኛ ትምህርት ቤቶች መጓጓዣን በተመለከተ ለተመረጡ የሳተላይት ፒካፕ ቦታዎች ሪፖርት የሚያደርጉ ይሆናል።

***በልዩ ስጠና ትምህርት ቤት የአንድ ቤተሰብ ልጆች ተማሪዎች***
የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት የአንድ ቤተሰብ ልጆች ተማሪዎች አሁን ተመዝገበው የሚገኙ ከአንድ ቤተሰብ የሆኑ ተማሪዎች ክፍላቸው ከቅድመ-መዋለ ህፃናት እስከ 4፣ 6 እና 7 የሆኑ ከሆነና ወላጆቻቸው ዚያው ትምህርት ቤት እንዲመዘገቡላቸው ከጠየቁ ቦታ መኖሩ ተረጋግጦ አንድ ትምህርት ቤት ሊመዘገቡ ይችላሉ። የአንድ ቤተሰብለ ልጆች ምደባ የማይቻል ከሆነ፣ እያንዳንዱ ተማሪ እጣው ሲወጣ ባላቸው ቅደም ተከተል መሰረት በተጠባባቂነት ይያዛሉ። **ይህ አካሄድ ለቅድመ መዋለ ህፃናት አመልካቾች ወይም በአሁኑ ጊዜ በ5ኛ እና 8ኛ ክፍል ተመዝግበው ለሚገኙ የአንድ ቤተሰብ ተማሪዎች ወይም የዘገዩ አመልካቾችን <u>አይመለከትም</u>።**

ለአንድ ትምህርት ቤት እና ለተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ የሚያመለክቱና ተመሳሳይ የልደት ቀን ያላቸው የአንድ ቤተሰብ አባላት፣ የወላጆች/የአሳዳጊ ምርጫ ከሆነ፣ ከልጆቹ አንደኛው ከተመደበ ሁሉም እንደተመደቡ ይቆጠራል። «ለልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት የሚያመለክቱትን እህትና ወንድሞች» ማሳወቅና ለእያንዳንዳቸው አስፈላጊውን መረጃ መሙላት የወላጆች/የአሳዳጊዎች ሃላፊነት ነው።

***በማመልከቻው ላይ የእህትማማችንትና የወንድማማችነት ሁኔታን ሳያሳዩ መቅረት ይህ አቅርቦት ለእህትማማቾች/ወንድማማቾች ተግባራዊ እንዳይሆን ያደርጋል። እያንዳንዱ ወንድም/እህት እንደ አንድ ተማሪ ለምዝገባው እድሉን/ሏን ይሞክራል/ትሞክራለች። ለእህትና የወንድሞች ቅድሚያ ለማግኘት፣ አንድ ወላጅ ለሁሉም እህትና ወንድሞች በተመሳሳይ የወላጅ መለያ ማመልከቻ ሊሞላ ይገባል።***

በዚህ ሰነድ፣ «እህትና ወንድም» ተብለው የሚወሰዱት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩና ተመሳሳይ ወላጅ(ጆች) ህጋዊ አሳዳጊነት የወሰዱባቸው ወይም ያላቸው የቤተሰብ አባላት ማለት ነው። ህጋዊ ሰነድ መቅረብ አለበት።

**የሙሉ ሰዓት ሰራተኞች ልጆች**
በዲስትሪክቱ ውስጥ የሙሉ ሰዓት ተቀጣሪ የሆኑ ህጋዊ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላሏቸው ልጆች ብቻ፣ የሚከተሉት አሰራሮች ተግባራዊ ይሆናሉ። እነዚህ አሰራሮች ከመዋለ ህፃናት በፊት ላሉ ፕሮግራሞች አይሰሩም።

ከልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች እና ከማግኔት ትምህርት ቤቶች ጋር በተገናኘ ከታች በአንቀፅ 3 እና 4 የቀረቡት እንዳሉ ሆኖ ፣ ህጋዊ አሳዳጊያቸው ወይም ወላጃቸው የዲስትሪክቱ ሙሉ ሰዓት ሰራተኛ የሆኑ ልጆች ወላጃቸው በሚሰሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲመዘገቡ ይፈቀድላቸዋል፤ **ወይም ልጁ/ጅቷ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም («አይ.ኢ.ፒ») ያለው/ላት ከሆነ፣ የልጁን/ቷን አይ.ኢ.ፒ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ በሚያደርግ ሌላ የዲስትሪክቱ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ይፈቀድላቸዋል።** ልጁ/ቷ ከመመዝገቡ/ቧ በፊት የተማሪዎች ምደባ ቢሮ ሊያውቅ ይገባል። የትራንስፖርት አገልግሎት በዲስትሪክቱ አይቀርብም። ሰራተኛውና ተማሪው በሌላ ዲስትሪክት የሚኖሩ ቢሆኑም እንኳ የመመዝገብ ክፍያ አይከፍሉም። ይህ አማራጭ ያለው ትምህርት ቤትን መሰረት ላደረጉ ሰራተኞች ብቻ ነው።

ከልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች እና ከማግኔት ትምህርት ቤቶች ጋር በተገናኘ ከታች በአንቀፅ 3 እና 4 የቀረቡት እንዳሉ ሆኖ ፣ ህጋዊ አሳዳጊያቸው ወይም ወላጃቸው የዲስትሪክቱ ሙሉ ሰራተኛ የሆኑ ልጆች ወላጃቸው በሚሰሩበት የመጋቢ ትምህርት ቤት እርከን ውስጥ እንዲመዘገቡ ይፈቀድላቸዋል፤ **ወይም ልጁ/ጅቷ አይ.ኢ.ፒ ያለው/ላት ከሆነ፣ የልጁን/ቷን አይ.ኢ.ፒ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ በሚያደርግ ሌላ የዲስትሪክቱ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ይፈቀድላቸዋል።** የማዕከላዊ ቢሮ ሰራተኞች ሰራተኛው ከሚሰራበት ጣቢያ በቀጥታ ባሉ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች እርከን ለሄዱ ይችላሉ። በዚህ ንዑስ አንቀጽ ስር የተገለፀውን እድል ለመጠቀም የሚፈልግ ሰራተኛ በሱፐርኢንቴንዳንቱ የተዘጋጀውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ባደረገና የዲስትሪክቱንና የግለሰቡን ለትምህርት ቤት ዝግጅቶች ለማድረግ የሚያስፈልገውን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተማሪዎች ምደባ ቢሮ ማሳወቅ አለበት፤ ለዚህም በተጨማሪነት፣ይህ የጊዜ ሰሌዳ በተቀጠሩበት ቀን የጊዜ ሰሌዳው ሊያካትታቸው የሚችላቸውን አዳዲስ ተቀጣሪዎችንም ሊያካትት ይገባል ለዚህም የጊዜ ሰሌዳው የመጀመሪያ ዓመት ፖሊሲው እስከሚተላለፍበት ያለውን ጊዜ በመጠቀም ማስተካከያ በማድረግ በ2019-2020 የትምህርት ዓመት መስፈርት የሚያሟሉ የወቅቱ ሰራተኞችን በሙሉ ማካተት አለበት። የትራንስፖርት አገልግሎት በዲስትሪክቱ አይቀርብም። ሰራተኛውና ተማሪው በሌላ ዲስትሪክት የሚኖሩ ቢሆኑም እንኳ የመመዝገብ ክፍያ አይከፍሉም። የመጋቢ ትምህርት ቤቶችን ሂደት እንዲጠቀሙ ከታች በተገለጸው መሰረት የሚፈቀድላቸው ተማሪዎች ተመዝግበው እንዲቀጥሉ በትምህርት ቤቱና በዲስትሪክቱ የጸደቁ የባህሪ መስፈርቶችን፣ አቴንዳንሶችን እና የጊዜ አከባበር ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

በእነዚህ ደንቦች መሰረት የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ለመከታተል የሚፈልጉ ልጆች የምርጫ ሂደቱን ማለፍና እንደየትምህርት ቤቱ የሚለያዩ የቅበላ ሂደቶችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። የትራንስፖርት አገልግሎት በዲስትሪክቱ አይቀርብም። ሰራተኛውና ተማሪው በሌላ ዲስትሪክት የሚኖሩ ቢሆኑም እንኳ የመመዝገብ ክፍያ አይከፍሉም።

**ለልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት የማመልከት ሂደት**
የግል ኮምፒዩተር፣ የአካባቢ ላይብራሪ ኮምፒዩተር ወይም ከትምህርት ቤት ምርጫ ፕሮግራሞች ቢሮ በመጠቀም በሚከተለው ድረ ገጽ ማመልከቻውን ይሙሉ **http://yourchoicedekalb.org**

የማመልከቱን ሂደት በቀነ ገደቡ ለማጠናቀቅ ሁሉንም ሰነዶች **ከማመልከቻው ጋር አብሮ** ማስገባት/መላክ የወላጅ/የህጋዊ አሳዳጊ ሃላፊነት ነው (የነዋሪነት ማረጋገጫ፣ የልደት ሰርተፊኬት፣ ሪፖርት ካርድ፣ ወዘተ)። ሁሉም ደጋፊ ሰነዶች ለትምህርት ቤት ምርጫ ቢሮ በቀነ ገደቡ ውስጥ እስካልቀረቡ ድረስ ማመልከቻዎ እንደተጠናቀቀ አይቆጠርም። **ሁሉም የሚገቡት ሰነዶች የዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ንብረት ይሆናሉ።**

በዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ውስጥ ያልተመዘገቡ አመልካቾች የነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል (ወቅታዊ የጋዝ፣ የኤሌክትሪክ፣ የውሃ ቢሎች፣ ሞርጌጅ ስቴትምንት፣ ወይም የሊዝ ስምምነቶች፣ በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ስም)። **የስልክ ቢሎች፣ የባንክ ስቴትመንቶች፣ የኬብል ቢሎች ወዘተ የነዋሪነት ማረጋገጫ ሆነው አያገለግሉም።**

በዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ውስጥ ያልተመዘገቡ አመልካቾችና ከቅድመ መዋለ ህጻናት እስከ አንደኛ ክፍሎች ለመመዝገብ የሚያመለክቱ ከሆነ ማመልከቻቸውን ለማጠናቀቅ የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው።

በዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት ውስጥ ያልተመዘገቡና በአሁኑ ጊዜ ከ1-7 ክፍል የሆኑ አመልካቾች የማመልከት ሂደታቸውን ለማጠናቀቅ በጣም የቅርብ ጊዜውን ሪፖርት ካርድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

**አውቶማቲክ የእጣ አወጣጥ/የአመራረጥ ሂደት**

የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት አመልካቾች፣ በየትኛውም ወይም በሁሉም የትምህርት ደረጃ የአመልካች ተማሪዎች ብዛት ተቀባዩ ትምህርት ቤት ካለው ቦታ በላይ እንደሚሆን  የሚጠበቅ ከሆነ በዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት የአስተዳደራዊና የማስተማሪያ ኮምፕሌክስ ውስጥ በአውቶማቲክ በሚደረግ የእጣ የምርጫ ሂደት ይከናወናል። ለምዝገባ ያልተመረጡ አመልካቾች ሁሉም አመልካቾች እስከሚመደቡ ድረስ በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ። **አውቶማቲክ የሆነው የምርጫ ሂደት በትክክል ያልሰራበት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ አውቶማቲክ የሆነው የምርጫ ሂደት እንደገና ይደረግና መጀመሪያ ላይ የተደረገው ምርጫ ወይም የተጠባባቂነት ዝርዝር በአዲሱ የምርጫ ሂደት መሰረት ሊቀየር ይችላል።**

**የቦታ ስርጭት**

**የመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቶች**
በእያንዳንዱ የትምህርት አመት፣ በእያንዳንዱ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ለእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ የሚኖረው ቦታ እጣ ማውጣቱ ከመከናወኑ በፊት ይወሰናል።

በቦርድ ፖሊሲ፣ ጄቢሲሲ መሰረት፣ ከመዋለ ህጻናት-5 የክፍል ደረጃ የሚገኙና ወላጆቻቸው በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሙሉ ሰዓት ሰራተኞች የሆኑ ልጆች ቦታ እስካለ ድረስ። ለሁሉም የሰራተኞች ልጆች የሚሆን ቦታ ከሌለ፣ አመልካቾች በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ።

እያንዳንዱ የመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ያለው ቦታ በዙሪያው ላሉ መጋቢ ትምህርት ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶቹ እንዳለባቸው የቦታ ጥበት ወይም የምዝገባ ብዛት መሰረት የሚከፋፈል ይሆናል። በእጣ ማውጣት በሚደረገው የምርጫ ሂደት የልዩ ስልጠና ሰራተኞችን፣ እህትና ወንድሞችን እና ቀሪውን ተመዝጋቢ ጨምሮ ሁሉም ተማሪዎች በሦስት ምድብ ይመደባሉ። ምደባ ያላገኘ ማንኛውም አመልካች በምርጫ ሂደቱ በሚወጣበት ቅደም ተከተል መሰረት በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ ይመደባል። እነዚህ የምርጫ መመሪያዎች ቅድመ መዋለ ህፃናት ፕሮግራሞችን አይመለከቱም።

**የመካከለኛ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት**
በእያንዳንዱ የትምህርት አመት፣ ለእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ የሚኖረው ቦታ እጣ ማውጣቱ ከመከናወኑ በፊት ይወሰናል።

በቦርድ ፖሊሲ፣ ጄቢሲሲ መሰረት፣ ከመዋለ ህጻናት-5 የክፍል ደረጃ የሚገኙና ወላጆቻቸው በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሙሉ ሰዓት ሰራተኞች የሆኑ ልጆች ቦታ እስካለ ድረስ። ለሁሉም የሰራተኞች ልጆች የሚሆን ቦታ ከሌለ፣ አመልካቾች በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ።

እያንዳንዱ የመጀመሪያ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ማህበረሰብ ለስድስተኛ ክፍል ያለውን ክፍት ቦታ እኩል በመከፋፈል የመካከለኛ ደረጃ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቱን 50% ይወስዳል። ሌሎች በአቅራቢያ ነዋሪ የሆኑ የመካከለኛ ደረጃ የትምህርት ቤት የመከታተያ አካባቢ አመልካቾች ቀሪውን ግማሽ የስድስተኛ ክፍል ቦታ ይይዛሉ። 50%-50% ምደባ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት አመልካቾችን በአቅራቢያቸው የሚገኝ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማግኘት እንዲችሉ ይፈቅድላቸዋል። ሌሎች በአቅራቢያ ነዋሪ የሆኑ የመካከለኛ ደረጃ የትምህርት ቤት የመከታተያ አካባቢ አመልካቾች ቀሪውን ግማሽ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል ቦታ ይይዛሉ። በእጣ ማውጣት በሚደረገው የምርጫ ሂደት የልዩ ስልጠና ሰራተኞችን፣ ተመዝግበው የሚገኙ እህትና ወንድሞችን፣ ቀደም ሲል የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቱ ተመዝጋቢዎችንና እና ቀሪውን ተመዝጋቢ ጨምሮ ሁሉም ተማሪዎች በአራት ምድብ ይመደባሉ። ያሉት የልዩ ስልጠና እና ቀሪ ክፍት ቦታዎች በተሳታፊ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ይከፋፈላሉ። እኩል መጠን ያላቸው ክፍት ቦታዎች ቢኖሩ፤ ቀሪዎቹ ቦታዎች በቦታ ጥበትና በምዝገባ ብዛት ምክንያት የበለጠ እፎይታ ለሚፈልጉት ጣቢያዎች ይከፋፈላሉ። የአመልካቾች ብዛት በማንኛውም ወይም በሁሉም ክፍሎች የመጋቢ ትምህርት ቤቶችን ክፍት ቦታዎች ብዛት ያለፈ ከሆነ አውቶማቲክ የሆነ የእጣ/የምርጫ ሂደት ይደረጋል።

**በመጠባበቅ ላይ ያለ ዝርዝር**
ሁሉም ክፍት ቦታዎች ከተያዙ በኋላ፣ በአውቶማቲክ የምርጫ ሂደቱ ያልተመደቡ አመልካቾች አውቶማቲክ ምርጫው በተደረገበት ሂደት እንደነበራቸው የምርጫ ቅደም ተከተል በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ የሚያዙ ይሆናል። የምርጫ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጨማሪ ቦታዎች የሚገኙ ከሆነ፣ ከተቀመጠው የተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ (በትምህርት ደረጃ፣ በመጋቢ ትምህርት ቤት) በአመልካቾች ይያዛል። የተጠባባቂነት ዝርዝሩ ልክ የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቱ አውቶማቲክ እጣ/ምርጫ ካበቃበት ቀን ጀምሮ እስከ **ኦገስት 31፣ 2019** ድረስ ተግባራዊ ይሆናል። የተጠባባቂነት ዝርዝሩ በትምህርት ቤት ምርጫ ፕሮግራሞች ቢሮ የሚቀመጥ ይሆናል። **ከኦገስት 31፣ 2019** በኋላ ተማሪዎች ! አይመደቡም። **ነገር ግን፣ ቅድመ መዋለ ህፃናት ውስጥ ያመለከቱ በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የጆርጅያን የቅድመ መዋለ ህፃናት ፕሮግራም የግዛት መመራዎች በመከተል ቦታ ሲገኝ በትምህርት ዓመቱ በማንኛውም ጊዜ ሊመደቡ ይችላሉ።**

**የማሳወቅ ሂደት**
በልዩ ስልጠና ትምህርት ቤቱ ዕጣ አሸናፊ የሆኑ አመልካቾች ማሸነፋቸው ይገለጽላቸዋል። ይህ ማሳወቂያ የምርጫውን ሂደት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ ቀሪ ሂደቶችን ለወላጆች ይገልፃል። በማንኛውም ምክንያት ወላጅ/አሳዳጊ የምዝገባውን ሂደት ሳያጠናቅቁ ቢቀሩ፣ የልጁ/ጅቷ ስም ከክፍል ዝርዝሩ ይወገዳል። የትምህርት ቤት ምርጫ ለማድረግ የተመረጡ ተማሪዎችን በሙሉ የሚከተሉት መመሪያዎች ይመለከቷቸዋል።

- አመልካች ተማሪው ለመግባት በተመረጠበት የትምህርት ደረጃ የሚያስፈልገውን መስፈርት ሳያሟላ ከቀረ፣ የተማሪው ምደባ ውድቅ ይሆናል። ቦታውም በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ ካሉት አመልካቾች ለቀጣዩ መስፈርት የሚያሟላ ተጠባባቂ ይሰጣል።
- ተማሪዎች የተመደቡበትን ቦታቸውን ለማስጠበቅ በተመደቡበት የልዩ ስልጠና ትምህርት ቤት ወስጥ በትምህርት መጀመሪያው ቀን ጀምሮ መገኘት ይኖርባቸዋል። ክፍት የሚሆኑ ቦታዎች ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ባሉ አመልካቾች ይሞላሉ።
- ከ**ኦገስት 31፣ 2019** በኋላ ማንም ተማሪ አይመዘገብም። ያልተመረጡ ተማሪዎች ለ2020 - 2021 የትምህርት ዓመት መልሰው ማመልከት ይችላሉ **ነገር ግን፣ ቅድመ መዋለ ህፃናት ውስጥ ያመለከቱ በተጠባባቂነት ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የጆርጅያን የቅድመ መዋለ ህፃናት ፕሮግራም የግዛት መመራዎች በመከተል ቦታ ሲገኝ በትምህርት ዓመቱ በማንኛውም ጊዜ ሊመደቡ ይችላሉ።** በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ የተቀመጡ ተማሪዎች በ2019 - 2020 አውቶማቲክ የዕጣ ማውጣት ሂደት የተሰጣቸውን የተጠባባቂነት ቁጥር የሚያካትት መረጃ ይደርሳቸዋል። በድረ ገፅ የሞሉ አመልካቾች የተጠባባቂነት ሁኔታቸውን በትምህርት ቤት ምርጫ ፕሮግራሞች የድረ ገጽ መለያ በመግባት ማየት ይችላሉ።
- የተመረጡት አመልካቾች ከፕሮግራሙ የምዝገባ ቀነ ገድብ በፊት የቀረበላቸውን ምደባ መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ አለባቸው።

# ማስገንዘቢያ

ዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ዲስትሪክት (ዲሲኤስዲ) በዚህ ህትመት ውስጥ በህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ የፕሮግራም መመሪያዎች፣ ቀኖች፣ ካሪኩለም እና ኮርሶች እንዲሁም በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ማንኛውም አገላለጽ ቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ ሳይኖርበት ለውጥ ሊያደርግ ይችላል።

ዲሲኤስዲ ቀድሚያ በማይታወቁ ሁኔታዎች ምክንያት ተማሪዎችን በማንኛውም የትምህርት ቤት ምርጫ ፕሮግራም ውስጥ ሊያስገባቸው መብት አለው።

ይህን ብሮሸር ሳያነቡ የሚቀሩ ወላጆች ወይም ተማሪዎች እዚህ ከተገለጹ ህጎችና ግዴታዎች ተጠያቂ ከመሆን አያድናቸውም።

በዲካልብ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ውስጥ በትምህርት ፕሮግራሞቹና በእንቅስቃሴዎቹ ወይም በቅጥር ትግበራዎቹ ሂደት እድሜን፣ ጾታን፣ ዘርን፣ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ የመጣብትን ሀገር፣ የአካል ጉዳት ሁኔታን ምክንያት በማድረግ አድሎ አለማድረግ በፖሊሲ የተቀመጠ ጉዳይ ነው።

DeKalb County School District